**አጭር መግለጫ**

# የዜጎች ቃል ኪዳን ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ
## Citizens Charter for a Democratic Ethiopia

*“ብሶት የእንቅስቃሴ ባህር ናት፤ የጠራች ራእይ የእንቅስቃሴ መርከብ ናት፤*
*ስልት ደግሞ የእንቅስቃሴ ሞተር ናት፤ ደፋር ዜጋ ግን ዋና አንቀሳቃሽ ነው።”*

**“የዜጎች ቃልኪዳን”** በመባል የምትጠራው የራዕይ ሰነድ በአስርት አመታት ዝግጅት: በብዙ አገር ወዳድ ባለሙያዎች ተሳታፊነትና፡ በሲቪክ ድርጅቶች አበረታችነት ተነደፈች። ዲሞክራሲያዊ ነጻ ዜግነትንና ማንነታዊ ኢትዮጵያዊነትን አንጋፋ መለዮዎች ያደረገች በመሆኗ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በባለቤትነት እንዲያስተናግዳት በአደባባይ የቀረበች ስጦታም ናት።

ዋና መልዕክቷም ‘ለማይገሰስ መብቱ ያልታገለ ሕዝብ ዲሞክራሲን ተጎናጽፎ አያዉቅም’ የምትለው ናት። አገራችን መስቀለኛ መንገድ ላይ ስለሆነች ዘላቂ የሆነ ህዝባዊ መዋቅር እንዲቋቋም ወቅታዊና ተጨባጭ እርምጃዎችን ለመውሰድና ለመንደፍ የሚያስችለን ራእይ ነው።

ለመንደርደሪያ ያህል ሁለት አንኳር ጥያቄዎችን እናንሳ፡- (1ኛ) የዜጎች ቃል-ኪዳን ለምን አስፈለገ፤(2ኛ) ይዘቱስ የሃገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ያህል ያስተጋባል፤ የሚሉትን።

## ሀ. ቃልኪዳን ለምን?

- አንዱ ያነሳሳን ግንዛቤ በኢትዮጵያዊነት ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ጸረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ሲያካሂዱ የቆዩት ፋታ የማይሰጥን የምንነት ዘመቻ ለመቋቋም ህዝባችንን የሚያስተሳስሩት ታሪካዊ፡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሃረጎች ረጅም መሆናቸውን በማሳየት የትብብር ጎዳና ለመክፍትና የሞራልና የትስፋ መላሸቅን ለመግታት ነው።

- ሌላው “ኢትዮጵያ ከየት ወዴት” የሚለው ዓብይ ጥያቄ ሲነሳ በደብዛዛነትና በተጻጻሪነት የሚቀርቡ ኣስተሳሰቦችን የሚያጠራ የጋርዮሽ “ራዕይን” አጉልቶ ለማቅረብ ነው። በተለይም ኢትዮጵያ የበላይና-የበታች ልማዳዊ የፖለቲካ ባህሏን የምትተውበት ኢንዱስትሪያዊ አድገትንና የከተማ ኑሮነትን ማስፋፋት ባለመቻሏ ዜጎቿ ራሳቸውን የስልጣን ባለቤት ወይንም ሉዓላዊ ኣድርገው ማሰብ እንግዳ ባህል ስለሆነ “የነጻ ዜግነትን” አስተሳስብንና ለማዳበርና በራስ-አምነትንና ህብረሰባዊነትን ለማጉላት ነው። “ሰማይ አይታረስ፤ ንጉስና ዳኛ አይከሰስ” የሚለው ዘይቤ መሽቶበት ጅብ እንዲበላውና የታሪክ መጻህፍት እንዲያብጠለጥሉት ዶልተንበት ነው ለማለትም ይቻላል።

- ቀጥሎም ሰፊ ደሃ ባለባት አገር ንቃትና ፍላጎት ካለው ለህዝባዊ ነጻነት ትግል በግንባር-ቀደምትነት የሚሰለፈው የተሻለ ኑሮ ያለው ዜጋ ስለሆነ ይህ ክፍል ራሱን በሲቪክም ሆነ በፖለቲካ ረድፍ አደራጅቶ በሰላማዊ መንገድ በድፍረት የሚጋፈጥበት ተልአኮዎችን፤ ስልቶችን ያካተተ ሰንደቅ-ዓላማን ለመለገስ ነው።

## ለ. ይዘቷስ?

ስለዚህ ይህ የዜጎች ቃለ መሓላ ታሪካዊና በጊዜያዊው የኢህዴግ መንግስት አድሎዋዊ አገዛዝ ላይ ባተኮረ ትችት ሳይዎሰን አጋራችን ተፈራራቂ አምባገነኖችን እንደጉንዳን ለምን ታፈላለች ብለን በመጠየቅ የሰፊው ሕዝብ ወደሚደግፈው ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ለመሸጋገር መታሰብ ያለባቸውን አንኳር ጉዳዮች ትዘረዝራለች።

የሕገ-መንግስታዊ ስርዓት ይዘቱ ብቻ ሳይሆን ሂደቱ የሕዝብን ባለቤትነትና ተሳታፊነት እንደሚጠይቅ ያስገነዝባል። ወደ ዲምክራሳዊ ስርዓት የሽግግር ወቅት ርዕሰ-ሕግ ሲረቅ የሚከተሉት አንኳር ጉዳዮች እንዲካተቱና እንዲተገበሩ ትጠይቃለች፡-

- ብሔርን ሆነ ሀይማኖትን የማያማከል ኅጠኛ መንግስታዊ ስርዓት እንዲያከትም፣
- ከሰፊው ህዝባችን የተውጣጣ ሁሉን ወካይ የሲቪልና የጸጥታ አገልግሎቶች፣
- ሚዛናዊ የመንግስት አውታሮች፣
- ውድድራዊ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ስርዓቶች፤
- የዜጎች ሉዓላዊነት ከመንግስት ሉዓላዊነት ቅድሚያዊነት፤
- የግለሰብ መብቶች ቀዳሚና ለቡድን መብቶች ምሰሶነታቸው፤
- ዜጎች በረሃብና በችግር ቸነፈር እንዳያልቁ መንግስታዊ ዋስትና መሰጠት፤
- አንድ ብሄራዊና አካባቢያዊ የስራና የትምህርት ቋንቋ አስፍላጊነት አንገብጋቢ ስለሆነ አማርኛ የመጀመሪያው በክፍለ-ሃገራት ሁሉ ቋንቋ እንዲሆን የሚሉ ናቸው።

## ሐ. ታዲያ ወዴት?

በሲቪክ ድርጅቶች ቀንደኛነትና አስተባባሪነት በወል መርሃ-ግብር የሚንቀሳቀስ ዓለም-አቀፍ “የአገርህን ኣድን” ንቅናቄ አንድማያስፈልግ ሁላችንም የዘመናችን ትእዛዝ መሆኑን አናምናለን።  የንቅናቄው አባል ለመሆን የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም አገር-ወዳድ ግለ-ሰቦች ከላይ በራእይ መልክ የተጠቀሱትን የአኢትዮጵያዊነት መርሆዎችን እንደምናቅፍና አገር ቤት ይሚካሄደውን መብታዊ ትግል ለመደገፍ ቃል ከገባን ቆይተናል።

የቀረውና ያልተመለሰው ዓብይ ጥያቄ በአንድ-ወጥ ድርጅት በህብረት ተሰልፈን የቻልነውን ያህል እናበረክታለን ወይንስ በመንደር ድርጅቶች ስብስብ በትንሹም በትልቁም በውስጥ ድርጅታዊ ሽኩታዋች ስናላዝን እናረጃለን ወይ የሚለው ጥያቄ ነው። ራእዩም ይሀው፤ ኢላማውና አላማው ይኀው፤ ሜዳውም ይኀው። ታዲያ የቀረን ፈረሱ ብቻ ነው እኮ! ፈረሱን በሚመለከት “ኢትዮጵያዊነት” በመባል የተዋቀረውን የአለም-አቀፍ ድርጅት ተልዕኮና ደንብ  እንዲሁም “ቃል-ኪዳኑን” በጥሞና እንዲመለከቱና በአባልነት ድጋፍዎን እንዲሰጡን በታላቅ አክብሮት እንጋብዛለን። ዲሞክራሲ በወረቀትና በዲስኩር ብቻ ሳይሆን በባለቤትነ፤በስራና በተሳትፎ ይገነባልና።

*ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ <u>የጋራችን</u>፤*
*ዘርና ኃይማኖት <u>የግል</u> ጌጦቻችን።*

Website:  http://www.ethiopiawin.net